# እራስዎን ይጠብቁ።

## የCOVID-19/ ኮሮናቫይረስ ክትባትን ይውሰዱ።



በCOVID-19/ኮሮናቫይረስ የሚከሰት የኢንፌክሽን ስጋትን በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀንሱ ክትባቶች ተገኝተዋል። በአሁን ወቅት፣ ለጤና እንክብካቤ ባለሞያዎች እና የመጀመሪያ እርዳታ ምላሽ ሰጪዎች ተደራሽነታቸው የተገደበ ነው፣ እና በ2021 ጸደይ ላይ ለአጠቃላይ ህዝቡ በስፋት ተደራሽ እንደሚሆን ይጠበቃል። ክትባቱ ሲገኝ መውሰድ የሚያስፈልግበት በርካታ ምክንያቶች አሉ። በጣም አስገዳጅ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ እርስዎን እና በዙሪያዎ ያሉትን ሰዎች ከዚህ ለህይወት-አስጊ ከሆነ ቫይረስ ሊጠብቅ መቻሉ ነው።

## የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ) ክትባትን መውሰድ የሚያስፈልግበት አራት ምክንያቶች

### 1 አስተማማኝ ነው።

በእነዚህ አስቸኳይ ሁኔታዎች FDA ክትባቶች እንዲለቀቁ ፍቃድ የሚሰጠው አስተማማኝ መሆናቸውን የሚያሳይ ዳታ እና አነስተኛ የጥራት ደረጃዎችን የሚያልፉ ወይም የሚያሟሉትን ብቻ ነው።

### 2 ውጤታማ ነው።

COVID-19/ኮሮናቫይረስ ለመከላከል በጣም ውጤታማ መንገድ ነው፣እና ባለሙያዎች በቫይረሱ ቢያዙም በጣም በጽኑ ከመታመም (ልክ እንደ ፍሉ(ጉንፋን)) ሊረዳዎ እንድሚችል ያምናሉ።

### 3 ነጻ ነው።

አቅራቢዎች ሰዎች የመክፈል አቅም ባይኖራቸውም ሊከትቧቸው ይገባል። አቅራቢዎች የቢሮ ጉብኝት ክፍያ፣ወይም የአስተዳደር ክፍያ ሊያስከፍሉ ይችላሉ፣ነገር ግን ይህ ክፍያ ከመድን ወይም ከ Medicare/Medicaid ሊጠየቅ ይችላል።

### 4 አነስተኛ የጎንዮሽ ጉዳቶች።

በክሊኒካዊ ሙከራዎች ውስጥ ክትባቱን በፈቃደኝነት ከወሰዱ ከ 70,000 በላይ ሰዎች በጣም ዝቅተኛ የጎንዮሽ ጉዳቶች ነበሩባቸው ፣ በጣም የተለመዱት መርፌ የተወጉበት ቦታ ክንድ ላይ ቁስል፣የተወሰነ ትኩሳት ወይም የሰውነት ህመሞች ናቸው።

## ስለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት ሌሎች ጠቃሚ ዝርዝሮች

- አብዛኛው የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባቶች ከፍተኛ መከላከልን ለመስጠት፣ በሶስት ሳምንታት ርቀት ይሰጣሉ፣ በጣም ጥሩ መከላከልን ለማቅረብ።
- ክትባቱ ለትልቅ ክሊኒካዊ ሙከራዎች ፈቃደኛ በሆኑ ከ 70,000 በላይ ሰዎች ላይ አስቀድሞ ሙከራ ተደርጓል።
- በተጨማሪ የክትባት አምራቾች የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ማህበረሰቦች፣ ጥቁር እና ሂስፓኒክ ግለሰቦችን ጨምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በክሊኒካዊ ሙከራዎቻቸው ውስጥ እንዲሳተፉ ጠይቀዋል።
- እርስዎ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ተመርምረው ፖዘቲቭ ከሆኑ፣መከተብ የሚኖርብዎ ስለመሆኑ የጤና እንክባክቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።
- እንደዚያም ሆኖ የህዝብ ጤና ሀላፊዎች ተቃራኒውን እስካልገለጹ ድረስ እንደ ጭምብል መልበስ፣ማህበራዊ ርቀት መጠበቅ፣እጅ መታጠብ እና ሌሎች የንጽህና ተግባሮችን የመሳሰሉ ሌሎች ጥንቃቄዎችን መተግበር አለብዎ።
- መጀመርያ ላይ ክትባቱ ህጻናት ወይም ነፍሰጡር ሴቶች እንዲጠቀሙት ላይመከር ይችላል። እነዚህ ቡድኖች እንዲጠቀሙ የሚያስችል ምክረሀሳቦችን በማካተት ወደፊት አሻሽሎ ለማቅረብ አምራቾች ሙከራ የሚያደርጉባቸውን ሰዎች ማስፋት ጀምረዋል።

ስለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ክትባት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ይጎብኙ, visit coronavirus.dc.gov/vaccine

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR